# ሳያዩ የሚያምኑ፤ ሳይሰሙ የሚያወሩ፤ ሳይናገሩ የሚኖሩ፤ ብጹዓን ናቸው ርሃብን ይችራሉና!

*ወያኔያዊ: አብዮታዊ ዲሞክራሲ ቁጥር 1 2003 ዓ.ም.*

*አሥራደው (ከፈረንሳይ)*



*አዲሱ ዓመት ........................................................ አልልም ይልቁንም፤ አዲሱ ዓእት ያበጠ የሚፈነዳበት፤ የከረረ የሚበጠስበት፤ የጠገቡ የሚራቡበት፤ የበደሉ የሚክሱበት፤ ዕውነት የምታሸንፍበት፤ የአገር ሃብት የዘረፉ የሚዳኙበት፤ በስልጣን የባለጉ የሚቀጡበት፤ የሕግ የበላይነት የሚሰፍንበት፤ ሕዝብ የሚከበርበት፤ በግፍ የታሰሩ ነፃ የሚወጡበት፤ ይሁንልን ብል ይሻላል ::*

*ለነገሩ ያህል አልኩ እንጂ አዲሱ ዓመት መጣ አልመጣ ለድሃው ወገናችን ምን ሊፈይድ? ሌላ የችግርና የችጋር ክምር ለመሸከም፤ በዘመነኞች የወጥ ሽታ አፍንጫውን በማስጠረብ የሆዱን ወስፋት ለማንጫረር፤ ሊቀምሰው በማይፈቀድለት የምግብ ምች ለመመታት፤ በዘመነኞች ሳቅና ጭፈራ ጆሮውን ለማደንቆር ካልሆነ በቀር ምን ሊተርፈው?*

*ዘውትር የኢትዮጵያን ሕዝብ የመከራ ቀንበር ለማክበድ፤ የችግር ዘመኑን ለማራዘም፤ የአንድነት መሰረቱን ለማናጋት፤ ክብሩን ለመናድ፤ ሰንደቅ ዓላማውን ለማጉደፍ፤ መብቱን ለመግፈፍ፤ እንጂ ለደህንነቱ፤ ለዕድገቱ፤ ለሰባዊ መብቱ መከበርና ለሠላም ያልመጡት፤ ያለ ሕዝብ ፍላጎት: በጠብ መንጃ ሃይል: በሕዝብ ጫንቃ ላይ ቂጢጥ ያሉት:*

ቅንድባሙ ጠ/ ሚንስትራችን ፡ ሰሞኑን « የአምስት ዓመት ዕቅድ ፡ እድገትና ትራንስፎርሜሽን (Transformation) » በሚል በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ መንስኤ ፡ ሕዝባችን ለተጨማሪ የኑሮ ውድነት መዳረጉን ሰንሰማ፤ ቀድሞውኑ በችግር አለንጋ እየተገረፈ ያለውን ወገናችንን ፡ እነሰህ ብለው ሌላ የችግር ጉርጓድ ቆፍረው ፡ በቁሙ ሊቀብሩት እደወሰኑ ተረዳን ::

አያልቅበት እሳቸው ምን ችግሯቸው ? ሁሉ በኛቸው፤ ሁሉ በደጃቸው፤ እስቲ በደደቢት በረሃ በነበሩ ጊዜ የነበረው ገጽታቸውን ተመልከቱና፤ የዛሬው ፊታቸውን ደግሞ ቃኙት፤ « ሰው ኑሮውን ይመስላል » ይላችኋል ይህ ነው :: ቀንተህባቸው ነው እንዳትሉኝ ፡ እሳቸውን ወይም እንደ እሳቸው ፡ ሆኜ ባለመፈጠሬ አምላኬን፡ በእጅጉ ነው የማመሰግነው ::

ዛሬ በምንሊክ ቤተ መንግሥት የግፍ ጮማ ይቆረጣል፤ በደም የተቀላቀለ ውስኪ ይንቆረቆራል፤ የበደል ከበሮ ይደለቃል፤ በጥጋብ ጮቤ ይረገጣል፤ ......ይጨፈራል፤ ይዘለላል :: በአንፃሩ ሕዝባችን የዕለት ጉርሱን አጥቶ ይዋትታል፤ ዕለት በዕለት ኑሮ ፡ የብረት ሸክም ሆኖበት ፡ ክብደቱ እየጨፈለቀው ለሞት ያጣጥራል፤ ይህ ሁሉ የወገን መከራ ለነሱ ምናቸውም አይደል :: በአንዲት ምድር እኩል ተፈጥሮ የኑሮ ሁለት ገጽታዎች ይሏችኋል ይች ናት !

ያውም በሃቅ ሰርተው ያገኙት ሃብት ሳይሆን፡ በአንድ ለሊት ጨረቃ ፡ በአገር ሃብት ዘረፋ የበለጸጉ ፡ ዘመናዊ ጊዜ ሰጠሽ የወያኔ መሳፍንት ሲንደላቀቁ ፡ አብዛኛው ህዝባችን በገዛ አገሩ የበይ ተመልካችና ፡ የነሱ ፍርፋሪ ናፋቂ እንዲሆን ተደርጓል ::

ወያኔ ሕዝባችንን አደንቁሮ፤ አደህይቶና አደንዝዞ ፡ እንደበርሜል እራቁቱን እያንከባለለ ለመግዛት እንዲያመቸው ፡ በየጊዜው በተግባር የማይተረጎሙ፤ ለሕዝብ ጥቅም የማይውሉ ፡ እቅድ ተብዬዎችን ይፈበርካል :: በቅርቡ አቶ መለስ ዜናቅዊ የአምስት ዓመት ዕቅድ ብለው (ቅዠት ብንለው ይሻላል) ያቀረቡትም ይኸው ነው ::

እስቲ ጥቂቶቹን እንመልከት፤

I. « የምንደራደረው አኩርፈው መሳሪያ ካነሱትም ካላነሱትም ጋር ነው »

II. « በ2002 ምርጫ እንደ ጃፓንና ቻይና ወያኔ (ኢህአዴግ) አውራ ፓርቲ ሆነ እንጂ የአንድ ፓርቲ አምባገነንነት አልተፈጠረም »

III. « ከአሁን በኋላ መተካካት ይኖራል »

IV. « ኢትዮጵያ በሚቀጥሉት አምስት አመታት ውስጥ ፡ ከዕሕል እርዳታ ተላቃ፤ ባለሁለት አሃዝ 14.9 በመቶ የኢኮኖሚ እድገት ታመጣለች »..... ወዘተ ፡ ናቸው ::

እስቲ አንድ ባንድ እንመልከታቸው፤

*በእርግጥ አቶ መለስ ሠላምን ይፈልጋሉ?? አይመስለኝም!*

*ጭነው ይጋልቧቸው የነበሩ ሆድ አደር ተቃዋሚ ተብዬ (ተለጣፊዎች) የጉዞ ምዕራፋቸውን ስላጠናቀቁ በነሱ ምትክ ሌላ ጭነው የሚጋልቡት አጋሠስ ብጤ ለማፈላለግ ያደረጉት ጥሪ እንጂ ከልብ የመነጨ የሠላም ጥሪ አይደለም።*

*አቶ መለስ በርግጠኝነት ሠላም ከፈለጉ፤ መጀመር ያለባቸው ሩቅ ሳይሄዱ ከቤት መሆን ነበረበት፤ ማለትም ጠመንጃ አንግታና ቦምብ ታጥቃ ሳይሆን ብዕር ጨብጣ፤ ሕግን ተንተርሳ፤ ለሕግ የበላይነት፤ ለፍትህና ለዲሞክራሲ በመቆሟ ብቻ ለወህኒ የዳረጓትን አንዲት ዕንስት የሕፃን ልጅ እናት፡ ብርቱካን ሚደግሳን በመፍታት ቢጀምሩ፤ እውነትም ለዕርቅና ለሠላም፤ ፊታቸውን ለማዞራቸው ምልክት ሆኖ፤ አኮረፉ ለሚሏቸውም በር ከፋች በሆነ ነበር። ነገር ግን አቶ መለስ የሠላም በርና መስኮቱን ክርችም አድርገው ዘግተው ሠላም እንፍጠር ሲሉ፤*

*ምን እሩቅ ቢሆኑ ይሰማል ድምጽዎ፤*

*ምን ጥቁር ቢበሉ ነጭ ነው አርዎ፤*

*በታቦት ቢምሉም አይቀርም መካድዎ፤*

*ጌታው አያ ጅቦ እንደምን ልመንዎ።*

*ብላ ሰጋትዋን ለአያ ጅቦ እንደገለጸችው አህያ ይሆንና፡ ተአማኒነት ያጣሉ።*

*አቶ መለስ ቃላቸውን የማያከብሩ፤ ዕምነት የማይጣልባቸውና፡ ስልጣን ወዳድ በመሆናቸው፡ በተቃዋሚነት የተሰለፉት ቀርቶ በራሳቸው ጎራ የተሰለፉትም የሚያንቀላፉት አንድ ዐይናቸውን ጨፍነው ሁለተኛው ዓይናቸውን ከፍተው ነው።*

*አንዱ የአቶ መለስ ትልቁ ማጭበርበሪያ፤ እራሳቸውና ሹሞቻቸው ከሕግ በላይ ሆነው ሕግ እየጣሱ፤ ያለፍርድ ሲያስሩ፤ ዲሞክራሲያዊ መብት ሲገፉ፤ የማሰብ፤ የመጻፍና የመናገር መብት እየገደቡ፤ ኮሮጆ እየገለበጡ፤ ከምርጫ ሕግ ውጪ በጠርናፊ አስጠርንፈው ሕዝብን በግድ እንዲመርጣቸው እያደረጉ ፤ ሌሎችን «ሕገ መንግስታዊ ሥርአቱን ተቀብለው፤ ዓላማቸውን በሠላማዊ መንገድ የሚያራምዱ ከሆነ» የሚሉት ፈሊጥ አላቸው፤ የምለውን እንጂ የምሠራውን አትመልከት እንዲሉ።*

*ሕገ መንግሥቱ ከሰማይ የወረደ፤ የእግዚአብሔር አሥርቱ ቃላት እንደሆነ አድርጎ፤ ዜጎችን ማስፈራራት ዐይን ያወጣ ፌዝ ነው።*

- *ለመሆኑ ሕገ መንግስቱ ለማን ነው የወጣው?*
- *ማን አወጣው?*

- ማን አጸደቀው ?
- እንዲያከብረው የሚገደደውስ ማን ነው ?
- የሚጥሱትስ እነማን ናቸው ብለን እንጠይቅ እስቲ?

በመሠረቱ ሕገ መንግሥቱ ፡ ወያኔ በደደቢት በረሃ የነደፈውን ፡ የትግራይ ሪፐፐልክ ግንጠላ ፡ ከግብ ለማድረስ ፡ ሻዕቢያና ወያኔ በጨጉላ ዘመናቸው፤ በግድ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የጫኑት ቀንበር እንጂ፤ ሰብአዊ መብቱን፤ የአገሩን ሉአላዊነት፤ ድንበሩንና ክብሩን የሚያስጠብቅ መሆኑን አምኖ በመቀበል ያላጸደቀው መሆኑን በተጨባጭ እያየን ነው ።

አቶ መለስ ድፍረቱ የላቸውም እንጂ፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ፤ ለዚሕ ሕገ መንግስት ያለህን የድጋፍ፤ ወይም የተቃውሞ ድምፅህን ስጥ ቢሉት፤ በነቂስ ወጥቶ ተቃውሞውን እንደሚገልጽ፤ ቅንጣት ያህል አልጠራጠርም ።

የሕግ የበላይነት ባለመኖሩ፤ የወያኔ ቱባ ቱባ ባለስልጣናትና ፡ የዝርፊያ ሸርኮቻቸው፤ ከሕግ በላይ ሆነው ፡ አገር ሲመዘብሩና ሕዝብ ሲበድሉ ፡ ሃይ ! የሚል ሕግ ጠፍቶ፤ ድሃው ሕዝባችን መብቴ ይከበርልኝ ብሎ በመጠየቁ ብቻ ሕጉ በሁለት በኩል ተሞርዶ (ተስሎ) ከአፎቱ እየተመዘዘ እንደቅጠል ይቀጥፈዋል ።

ታዲያ የሕግ የበላይነት በማይከበርበት፤ የፍትህ ተቋማት ከመንግሥት እጅ ነፃ ባልሆኑበት፤ ጥቂት ዘረኞች በሚምነሸነሹበት፤ አንድ አንባ ገነን የፖለቲካ ድርጅትን ወያኔ (ኢህአዴግ) በተንሰራፋበት አገር ፡ « ሕገ መንግሥቱን ተቀብለውና አክብረው » የሚሉት የአቶ መለስ አስቂኝ ድራማ ከራሳቸው በስተቀር ማንንም ፈገግ አያሰኝም።

ሌላው ፡ አቶ መለስ ለማደናገር የሚንጠራወዙበት፡ ሕገ መንግሥት ተብዬ፤ ሕዝቡ ጥቅሙንና የአገሩን ሉአላዊነት ፡ የማያስከብር ሆኖ ካገኘው ፡ ሊያሻሽለው፤ ሊሰርዘው፤ ሊደልዘው፤ ጭራሹንም ሊሽረውና ሊለውጠው ፡ እንደሚችል ሊረዱት ይገባል ።
ሕገ መንግሥት ሕግ እንደሆነ መቀጠል የሚችለው፤ የአብዛኛውን ሕዝብ መብትና ጥቅም፤ የአገሩን ሉአላዊነት፤ የሕዝቡን አንድነትና ሰባዊ መብቱን ሲያስጠብቅለት ብቻ ነው ።

« አውራ ፓርቲ ተፈጠረ እንጂ የአንድ ፓርቲ አምባገነንነት አልተፈጠረም »ይሉናል፤

መቼም አቶ መለስ ፡ በግን ፡ በግ ናት ፡ ብሎ ለመጥራት፤ አንዲት ፀጉራም እንስሳ ፡ ከወደ ኋላዋ የሚንጠለጠል ነገር ያላት፤ አልፎ አልፎ ባ!ባ! እያለች የምትጮህ፤ እያሉ የሚያቀርቡት ነብስ የሚያሳምም ማደናገሪያና አዋቂ ለመምሰል በተናገሩ ቁጥር የሚደነጉሩት የፈረንጂኛ ቃል ትዝብት ውስጥ እንደሚከታቸው አይረዱትም ።
ለምሳሌ ትራንስፎርሜሽን፤ (Transformation) የሚለውን ቃል ብንወስድ አቻው ቃል ለውጥ የሚለው ሆኖ ሳለ ለምን ፈረንጂኛውን መደንጎር እንደመረጡ ሰናጤን፤

*አዲስ ነገር የፈጠሩ በማስመሰል ያልተማረው ወገናችንን ለማደናገር ካልሆነ በቀር ምንም ፋይዳ የለውም ::*

*99.6 በመቶ አሸናፊ ሆነ የሚሉት ፓርቲያቸውን: አንባ ገነን አለመሆኑን ለማስረዳት ፤ ወደ ጃፓንና ቻይና ተጉዘው ለመቧጠጥ የሞከሩት ተምሳሌት እንዳው አልኩ ለማለት ካልሆነ በስተቀር ቋት አይሞላም::*

*« ከአሁን በኋላ መተካካት ይኖራል » ይሉናል አቶ አያልቅበት፤*

*መተካካት ለሚለው ቃል፤ ትርጉም ወይም አቻ የሚሆኑት :ቃላት  መፈራረቅ፤ መቀያየር፤ መቀባበል፤ መለዋወጥ፤ ተራ በተራ፤ ማለት ሲሆን፤ እዚህ ላይ የምንረዳው የወያኔ ዘራፊ ሹማምንት የኢትዮጵያን ሕዝብ ገና ምን አይተሀ ? እየተፈራረቅን፤ እየተቀያየርን፤ ተራበተራ እንደ ፈረስ እንጋልብሃለን፤ ወይም እንደኳስ እየተቀባበልን እንለጋሃለን፤ በሌላ አነጋገር እንገዛሃለን ማለታቸው ሲሆን: የኢትዮጵያን ሕዝብ ምን ያህል እንደናቁት መታዘብ ይቻላል ::*

*« ኢትዮጵያ በሚቀጥሉት አምስት አመታት ውስጥ: ከዕሕል እርዳታ ተላቃ፤ ባለሁለት አሃዝ 14.9 በመቶ የኢኮኖሚ እድገት ታመጣለች » አሉን፤*

*እስቲ ወገኖቼ እግዜር ያሳያችሁ፤*

- *90% ሕዝባችን ድሃ በሆነበት አገር፤*
- *70% የሚሆነው ወጣት ሥራ አጥ በሆነበት ዘመን፤*
- *ከ6 እስከ 8 ሚሊዮን የሚቆጠሩ ወገኖቻችን በማያቋርጥ ረሃብ እየተሰቃዩ፤*
- *16 ሚሊዮን ሕዝብ ረሃብተኛ በሆነባት አገራችን፤*
- *የውሃና የኤሌክትሪክ ግልጋሎት በፈረቃ በሆነበት፤*
- *ሕዝባችን ያልተጠቀመበትን የውሃና የመብራት ፍጆታ በግድ እንዲከፍል በሚገደድበት የዘረፋ ዘመን፤*
- *ሰው ቢታመም ታክሞ በማይድንበት አገር፤*
- *ጥቂት በስልጣን የባለጉ ዘረኞች: በአመት ከ3 ቢሊዮን ብር በላይ በብድር የሚገኘውን ገንዘብ እየመዘበሩ በሚንደላቀቁባት፤ አብዛኛው ሕዝባችን የመከራ ኑሮ በሚገፋበት አገራችን ኢትዮጵያ: የማይጨበጥ አጉል ተስፋ ድንጋይ ዳቦ ይሆናል ! በአራዳ ልጆች አባባል ረገጣ፤ ወይም ሂድ እንግዲህ ! ካልሆነ ምን ይባላል ??*

እንዳው በጥቅሉ፡

ከትናንቱ ዛሬ ይሻለኛል ብዬ፤
ስንዴ እለምናለሁ መለስን አዝዬ።

ሆነብንሳ ጃል!

ወደው አይስቁ! አሉ ዕመት ማዘንጊያሽ።

ማሳረጊያ፡

እንግዲህ ወገኖቼ፡ ከወያኔ ጡጫ፤ ከጠገበ ርግጫ፤ ከባለጌ ግልምጫ፤ ከጉቦኛ ዳኛ፤ ከቀጣፊ ካድሬ፤ ከዘራፊ ባለስልጣንና፤ ከስንዴ ልመና፤ የምንላቀቀው እያንዳንዳችን፡ በአንድነት ለጋራ ጥቅማችን፤ ለእድገት፤ ለዲሞክራሲ፤ ለፍትህና ለሠላም መገኘት፡ አብረን ስንነሳና፡ ቆርጠን ስንታገል እንጂ፡ በፍራቻ፤ በውክልና ትግል፤ እኔ ተቀምጬ እነሱ ታግለው፡ ነፃ ያወጡኛል፤ በሚል በሃሞተ ቢስኝነትና በጨለምተኛ ምኞት ሳይሆን፤ ከያንዳንዳችን በሚፈልቅና በሚቀናጅ፡ ዕውቀት፤ ገንዘብ፤ ጊዜ፤ ድንጋይ፤ አሸዋና ሲሚኒንቶ፤ በምናፈሰው ላብና ደም የሚገነባ በመሆኑ ቆርጠን እንነሳ።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!

እግዚአብሔር ኢትዮጵያና ሕዝቧን ይባርክ!!

መስከረም 1 2003 ዓ.ም. (Septembre 11/ 2010)